# 9. ለተለዩ ብዱኖች የሚሰጥ የጤና እና የድጋፍ አገልግሎቶች

በኲንስላንድ፡ በተለይ በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉት ልዩ የሆኑ ቡዱኖችን ፍላጎት ለሟሟላት ያለሙ ብዙና የተለያዩ ዓይነት የጤና ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች አሉ።

በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የሚሰጡ ናቸው። ከነዚህ ዋናዋና የሆኑ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች እታች በዝርዝር ተጽፈዋል፥

### 13HEALTH (13 43 25 84)

- ብቁ የሆነ የጤና ምክር ያቀርባል
- በመንደሩ ውስጥ ለመደወል የሚከፈለው የቴሌፎን ክፍያ ያህል በመክፈል ብቻ፡ በ7 ቀናት ውስጥ 24 ሰዓቶች ሙሉ መደወል ይቻላል
- አስተርጓሚ ከፈለጉ፡ እንዲሰጥዎት ይጠይቁ።

### መዲካል ኤይድ የገንዘብ ድጋፍ (Medical Aids Subsidy Scheme)

- ሁል ጊዜ እና ቋሚ የሆነ ሁኔታ ወይም የአካል ጉድለት ላለባቸው የኲንስላንድ ነዋሪዎች፡ የሳብስድይ ድጎማ፣ የመግባባት ችርግ ላለባቸው ሰዎች የመግባብያ መሳርያ፣ የሽንት ችግር ላለባቸው መሳርያ፣ የእለት ኑሮ ኢርዳታ፣ ለእግር የሚደረግ የህክምና እንክብካቤ፣ የመንቀሳቀስ እርዳታ፣ ኦርተስስ እና ኦክስጅን የመሳሰሉት እርዳታ ይሰጣል።
- የMASS አገልግሎት ማእከል (07) 3250 8555 የሚለውን ያነጋግሩ

### ስፔክታክል ሳፕላይ ስኪም (Spectacle Supply Scheme)

- ለሚገባቸው የኲንስላንድ ነዋሪዎች፡ ነጻ የሆነ እና ብዙ ነገር የሚያጠቃልል መሰረታዊ የሆነ የሐኪም የዓይን መነጽር ትእዛዝ ይሰጣል
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ 13 HEALTH መስመር 13 43 25 84

## ልጆች እና ወጣቶች

### ፕራይማርይ ኬር ፕሮግራም (Primary Care Program)

- ከ 0-12 ዕድሜ ላሉ ሰዎች ሰፋ ያለ የጤና ፕሮግራም ይሰጣል
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ የልጅ የጤና መስመር (07) 3862 2333 ወይም 1800 177 279 (ከብሪስባን ውጪ)

### የኢሙኒዜሽን ክሊኒክስ (Immunisation clinics)

- የልጅ የጤና ክሊኒኮች፡ አንዳንድ የአከባቢ ካውንስሎች እና የቤተሰብ ሐኪሞች ለህጻናትና ልጆች ነጻ ክትባት ይሰጣሉ
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ የልጅ የጤና መስመር (07) 3862 2333 ወይም 1800 177 279 (ከብሪስባን ውጪ)

### ጤናማ የሆነ የመስማት ፕሮግራም

- በኲንስላንድ የተወለዱ ህጻናት በሙሉ፡ የጀሮ ምርመራ ያገኛሉ። ህጻኑ ይንም ምርመራ ካላለፈ፡ ወደ ሌላ ሕክምና እንዲላክ ይደረጋል
- በዚህ ቁጥር ይደውሉ፥ (07) 3131 6814 Statewide Coordinator
- http://www.health.qld.gov.au/hearing/translated_brochures.asp በ 19 ቋንቋዎች የተዘጋጀ መረጃ

### የልጆች እና የወጣቶች የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች

- ከ 0-18 ዕድሜ ላይ ሆነው እና የአእምሮ ጤና መታወክ ላላቸው ልጆች፡ በሆስፒታል እና የኮሚኒቲ አገልግሎቶች ነጻ የሆነ የምክር ጊዜ፣ ምርመራ፣ ሕክምና፣ እና እንክብካቤ ይሰጣል
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ Queensland Transcultural Mental Health Centre (07) 3240 2833 or 1800 188189 (ከብሪስባን ውጪ)

### የልጆች እርዳታ መስመር

- ልጆች በስልክ ቁጥር 1800 551 800 በመደወል በቀን 24 ሰዓት ሙሉ ነጻ እርዳታና ምክር ያገኛሉ

## ሴቶች

### የእርጉዝ ሴቶች (Maternity) አገልግሎቶች

- የህጻናት እንክብካቤ ብዙ ጊዜ በየቤተሰብ ሐኪምዎ (GP) ይጀምራል፡ እሱም ወደ ሆስፒታል፣ የመዋለጃ ማእከል፣ ወይም ሌላ የእርጉዝ ሴቶች እንክብካቤ ማእከል ይልክዎታል

### ተንቀሳቃሽ የሴቶች የጤና አገልግሎት

- በ 15 ልዩ ስልጠና የወሰዱ እና በኲንስላንድ መንደሮች እና ክፍለ ሀገሮች የሚሰሩ የሴቶች የጤና ነርሶች የቀመ ነው
- የበለጠ መረጃ ለማግኘት፥ 13 HEALTH መስመር 13 43 25 84

### በኲንስላንድ የጡት ምርመራ

- ከ40 ዓመት በላይ ለሆኑ ሴቶች በተለይም ከ 50 እስከ 69 ዓመት የሆኑ ሴቶች ነጻ የጡት ምርመራ (የማሞግራም ምርመራ) ይሰጣል። የጡት ምርመራ የጡት ካንሰር ለመመርመር ተብሎ ይደረጋል
- በዚህ ቁጥር መደወል ይችላሉ፥ 13 20 50 ከማንኛውም ስፍራ በኲንስላንድ ሆነው ቀጠሮ መያዝ ይችላሉ